# እውቀት እና ሥልጣኔ፥ ማንነት እና ድኅነት

## መግቢያ

ስለ ምድራዊ እውቀት አመጣጥና አካሄድ ስናስተውል፥
ባንድ በኩል ምድራዊ ሕይወታችንን ሲያሻሽል፥
በሌላም በኩል መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሲያጣጥል፥
ሙሉ ሆኖ የተፈጠረን ሰው እንዲህ ከሁለት ሲከፍል፥
ምድራዊ እውቀት እና የዘመኑ ሥልጣኔም ትርጉም ያጣል።

የሰው ኑሮ ከራሱ በመነጨ እውቀቱ እንዳይሆን፥
በራሱ ካገኘው እውቀት ውስጥ ጣልቃ የገባውን፥
ተፈጥሮአዊ ማንነቱን የወሰደበትን - ወይንም አደናብሮ የቀየረበትን፥
እስቲ እንመልከተው፥ የሰውን ምድራዊ እውቀቱን፥
ከጥንት ከአመጣጡ ጀምረን፤
ከጻዲቁ ሄኖክ መልእክትና አቤቱታ ተነስተን።[1]
እንዲሁም እንመርምር ታሪካዊ ሂደቱን፤
እውቀታችን በኛነታችን ላይ ያስከተለውን - ተፅንአውን።
በመጨረሻም፥ ኃይልና ሥልጣን፥ የእግዚአብሔር መሆኑን አውቀን፥
ድኅነት የሚገኝ ከእርሱ መሆኑን አምነን፥
ፍቅር፥ ሰላም፥ ጤንነትና ደስታን እንማጸናለን።

## ከዘመኑ እውቀት የጥቂቱ አመጣጥና ጉዳቱ

በጠፈር ውስጥ ሁሉ ነገር እርስ በርሱ እንደሚያያዝ ይታወቃል፤
እንዲሁም ጊዜ አካልን ተጣምሮታል።
ነፍሳማው ባለ ሕይወት ራሱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲያሻሽል፥
ግዑዝም እንዲሁ ሲለወጥ በአካል፥
አሮጌው በአዲሱ ይተካል፤
<u>መለ</u>ወጥ - አንጻራዊ እድገትም ይኖራል፤
በዚሁም አንጻር፥ በእውነት ጎዳና ትይዩ የውሸት ጎዳና ይከፈታል።
በቀጥተኛ እድገት - በተፈጥሮአዊ ሁለንተናዊ መሻሻል፥
በመንፈሳዊ - ሞራላዊ - ኑሮአችን ውስጥም ክፋት ጥልቅ ይላል።
የክፋት መንፈስ (እርኩስ መንፈስ) ነው ጠላታችን፥ ጣልቃ እየገባ የሚያሰናክል፥
የሰው ሥልጣኔም መጨረሻው እልቂት እንዲሆን የሚታገል።

አለም ከተፈጠረች ጀምሮ - እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከደብዛዛው ወደ ደመቀው አምርተዋል፤
ከጥፋት ውሃ በፊትና በኋላ፥ የተለያዩ ምድራዊ ሥልጣኔዎች ብቅ ብቅ ብለዋል፤

---

[1] “አቤቱ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥ የአፌ ቃልና የልቤ ሃሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።” መዝ. 18 (19)፡ 14

አንድ አይነት ሥልጣኔ ሲወድም፥ ከቀድሞው ለየት ያለ ሥልጣኔ ተተክቷል፤
ሰውም በጊዜ ውስጥ ህልውናው እንዲጸናለት - እንደጊዜው ራሱን እየቀያየረ መጥቷል።
መቼስ ሰው በኑሮው ከፍና ዝቅ ሲበዛበት ይጨነቃል፤
በእውቀት መራቀቅ ሲያበዛም ማንነቱን ይረሳል።
አንድ ትውልድ አልፎ ሌላው እንኩኣን ሳይከተል፥
እንዲሁ ከሆነው ወዳልሆነው እየማለለ ይኖራል።
በዚህች ምድር፥ የእውቀት ዘለአለማዊ እውነታዊነት በማይታይበት፥
እነሆ! ከጥንት ከሄኖክ ጀምሮ በጻድቃን የተላለፈ አንድ መልእክት፥
የሚሆነን ትምህርት - አንባቢ እንደየአመለካከቱ የሚጠቀምበት።
በጥንት ዘመን - ከኖህ የጥፋት ውሃ በፊት፥
አንድ ኢትዮጵያዊ )ኤርትራዊ( ይኖር ነበረ - ሄኖክ የሚሉት።
ሄኖክ - የያሬድ ልጅ፥ የማቱሳላ አባት፥
የላሜህ አያት፥ የኖህ ቅድመ አያት[2]፥
በጠፈር ተመላለሰ፥ ከዚያም አስተዋለ - ተፈጥሮአዊ ክስተት፥
ለኛም አቆየልን - ሞራላዊ ምክር - የሚሆነን ትምህርት።
ሄኖክ እኛን ወንዶችን ሴቶችን - ወልዶ ተሰወረ፤
በምድራችን በሚሰራው መጥፎ ሥራ ሁሉ እንደተማረረ፥
ለእግዚአብሔር አቤቱታ እያሰማ ከዚያው ቀረ።
እስቲ ለኣንድ አፍታ አወቅን የምንለውን ሁሉ እንርሳው፥
ሄኖክ የሚለውን ብቻ እንስማው፡-
“ሰውም በምድር በበዛ ጊዜ፥ ቆነጃጅቶች ሴቶች ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር ከመሃላቸው፤
አንዳንድ መላእክትም ይህንን ክስተት ሲያስተውሉ ቆይተው፥
ሴቶቹን ለማግባት ወሰኑ በውበቶቻቸው ተማርከው።
እነኚህ ከደበረ ቅዱስ[3] የፈለሱ መላእክት፥ ስሙ እስማዚያ መሪያቸው፥
ቆንጃጅት ሴቶችን እየመረጡ አገቧቸው፤
ከነርሱም ወለዱ - የሰውን ልጅ ስርአቱን በጥሰው።
እነኚህ ኃጥአን መላእክት ከፈጣሪያቸው ፈቃድ ወጥተው፥
የራሳቸውን ስሜት በመከተላቸው፥
የተረገሙ ሆኑ ልጆቿቸው፥
እጅጉን ግዙፋን እየሆኑም በማደጋቸው፥
እስከ ሦስት ሺህ ክንድ ይደርስ ነበር ቁመታቸው።[4]
እርስ በርሳቸውም ተበላልተው አለቁ፥ የምድር ምግብ ስላልበቃቸው።”
ካሁን በፊት ግዙፋን (ረዓይት - ኔፊሊም) በምድራችን እንደተመላለሱ[5]፥
አንዳንድ ምልክቶችን ትተው፥

---

[2] ዘፍ. 5፡ 18-32

[3] ከመጽሕፍ ቅዱስ (የኦርቶዶክስ) መጽሐፈ ሄኖክ ከምዕራፍ ሁለት ጀምሮ..

[4] ሄኖክ 2፡ 12

[5] ዘፍ. 6፡4

ይህንን ለታሪክ ተመራማሪዎች ትተን እንለፈው።
ሄኖክ ኃጥአን መላእክትን የከሰሳቸው፥
መጥፎ እውቀትን በማስተላለፋቸው፥
እንዲሁም በብልግናቸው።
ለሰው ልጅ ያስተላለፉት "እውቀት" እንደየከነታቸው፦
"ሰይፍና ሾተል፥ ጋሻና ጥሩር መሥራትን፥
በዕንቁ ማጌጥን፥ እንሶስላ መሞቅን፥
ዐይን መኩኣልን፥ ቅንድብ መሸለልን፥
ምታት ማሳየትን፥ ሥር መማስን፥
ጋኔን መሳብን፥ ሟርትና ምታት ማሳየትን፥
የጨረቃን አካሄድ፥ ኮከብ መቁጠርን፥
ሌሎችም ለሰው ያልተገለጡ - ከምድር የተሰወሩትን።
እንዲህም እያስተማሩ - አመነዘሩ፤
ብዙ ዝሙትም አደረጉ - ወደ ጥፋትም ኣመሩ፤
በምድሪቱም ደምን ኣፈሰሱ፥ ግፍን ሰሩ፤
ሰዎችም ጮኹ፥ ድምጻቸውም ተሰማላቸው፤
ሚካኤል፥ ገብርኤል፥ ሱራኤልና ዑራኤል ደረሱላቸው፤...."
ሆኖም፥ የጥፋት ውሃ ሆነ መጨረሻው።
እንዳው በደምሳሳው ስንመለከተው፥
የሰው እውቀቱም ይሆናል፥ ኃጢአትና ግፍ መሥራትን ያባባሰው፤
ከመንፈስና ከሥጋ የተወለዱ ረዓይት - የከፋት መናፍስት ስማቸው፥[6]
ከፋትን ለሰው አውርሰው፥
በእውቀቱም ውስጥ ጨምረው፥
ሰውን አልተለዩትም በሥጋም ባይሆን በመንፈሳቸው።
እና - የሰው ልጅ የእውቀቱ ምንጭ - ከትውልድ ትውልድ የተላለፈው፥
በእውነት ይህ ከሆነ መነሺያው፥ ምን ነበረ፥ ሄኖክ የፈራው?
በኃጥአን መላእክት እውቀት ነው፥ ተለውጠን ከዚህ የደረስነው?
የከፋት መናፍስትም አብረው - ሰውን መስለው፥
የነርሱን ስነእመከኖአዊ አስተሳሰብ በሰው ጭንቅላት አስገብተው፥
እስከ ዛሬም ካልተለየን ከእነርሱ የተማርነው፥
ከዘር ዘር ተላልፎ እኛንም ወደ ከፋት የመራው፥
በጥንቱ ሥልጣኔ የታቀፈ ከፉው ነው?
እስቲ ይህንንም ከግንዛቤአችን አስገብተን እንመርምረው።
ከዘመኑ እውቀት ውስጥ በብዛትም ባይሆን በጥቂቱ፥
ከትእዛዝ ኣፍራሽ መላእክት የተላለፈ ስለሆነ ገና ከጥንቱ፥
መንፈሳዊነት የጎደለው - ተንኮል አዘል መሠረቱ፥
በእውቀታችን ውስጥም ጣልቃ በመግባቱ፥
ለዚህም ይሆናል፥ በምድራችን የጻድቃን ቁጥራቸው ያልበዛው?
የቀጥተኛ - የእውነተኛ ሰው ቁጥር ያነሰው፥
አንዱ ሲያለማ፥ ሌላው የሚያጠፋው።

---

[6] "አሁንም ከመንፈሥና ከሥጋ የተወለዱ ረዓይት በምድር ላይ ከፉዎች መናፍስት ይባላሉ።" ሄኖክ 4፡40

የከፋት መንፈስ ባለቤቱ፥ ሰይጣን[7]፡- (ጠላት - ምቀኛ - ሸረኛ)፥ ሰላማችንን አሳጥቶናል፤
እኛኑ መስሎ - በላያችን ነግሦ ይጫወትብናል።
"ሄኖክም እግዜብሔርን ደስ ስላሰኘው ሰወረው"፥[8]
ከሥራው ብዙ ሰይጣን ተንኮል ሊጠብቀው።
ኃጥአን መላእክት መንፈስ በመሆናቸው፥
እነርሱ አስተማሪዎች ሆነው፥ እኛኑ መስለው - ሳናያቸው፥
እንደ ደግ አሳቢ - ሲያበረታቱን በተንኮላቸው - ከውስጣችንም ተራብተው፥
እንዲህም ስለቆየን መስለናቸው፥ ስነ አመክኖአዊ ኣስተሳሰባችንም ተለወጠላቸው፤
አለማችንም በነርሱው አለም ተካተተላቸው።[9]
ክርስቶስም ክፉ አሳቢ ሰዎችን - የክፋት መንፈስ ስለ ተጠናወታቸው፥
“እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች”[10] ብሎ ስም አወጣላቸው፤
“የነቢያት ገዳዮች ልጆች...”[11] ብሎ ጠራቸው።
መጥምቀ መልኮት ቅዱስ ዮሐንስም፥ እነኚህኑ ክፉ አሳቢ ሰዎች፥
የከፋት መናፍስት ልጆች፥
“...እናንት የእፉኚት ልጆች..፥” አላቸው።[12]
በአንድ አለም ሁለት አለም በመኖሩ፥ በሰብእነታችን ጥርት ብለን አልተገኘን፤
የሁለት አለም ፍትጊያም ስላልቀረ፥ ችግሮች ተደራረቡብን፤
ለይተን ባላወቅነውና ባልተገነዘብነው ተንገላታን።
አንዳንድ መንፈሳዊያን ግን፥ ቀጥኛው ትምህርት - የሄኖክም አቤቱታ የገባቸው፥
ገዳም ገብተዋል፤ ከፍትጊያው አምልጠው፤
ከሩቅ ሆነው ያስተውላሉ፥ ሰብእናቸውን አስከብረው፤
በጾም በጸሎት ይተጋሉ፥ ምድራዊ ኑሮ አስጠልቷቸው።
በመንፈስ ምጥቀት ለተመለከተው (ወይንም ለሚታየው)፥
የከፋት መንፈስ በውስጣችን ጎጆ መስርቶ - አብሮን ነው የሚኖረው።
ተፈጥሮአዊ ክስተት የራሱ ሂደት እንደሌለው፥
ወይንም ተፈጥሮአዊ ክስተትን ተከትሎ የሚሄድ ተስፋ እንደሌለው፥
ጥሩውን መጥፎ - መጥፎውን ጥሩ የሚያስመስል አታላይ ነው።
እኛ ዛሬም እውቀታችን ብለን በኩራት የተቀበልነው፥
ማንነታችንን ያሳጣን - ሰብእናችንን የቀየረው፥
ያ - የደብረ ቅዱሳን ትምህርት፥ ሄኖክ ያጥላላው - መጥፎው፥

---

[7] “አንተ በንጋት የሚወጣ የአጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! ወደ አሕዛብም መልእክትን የላክህ አንተ ሆይ! አንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቀጠቀጥህ.......” ኢሳ. 14፡12

[8] “ሄኖክም እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘው አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ሰውሮታልና።” ዘፍ. 5፡24

[9] ከምድራዊነታችን ባሻገር ቅፅ አንድ ክፍል ሦስት - ከዚሁ ድረ ገጽ።

[10] ማቴ. 23፡33፥ ማቴ. 3፡7፥ ማቴ 12፡34

[11] ማቴ. 23፡ 41

[12] ሉቃ. 3፡7

ከጦር ግንባታ ትምህርት መጥቆ የወጣው፥
ተፈጥሮአዊ ሂደትን በመቀለስ ላይ የሚገኘው፥
እሱን ነው እኛም፡- “ሥልጣኔ - ሥልጣኔ” እያልን ያሞካሸነው።
ከመሠረቱ - ከፍቅር ያልተጀመረ፥
ሰዎችን በትእቢትና በትምክህት የወጠረ፥
መንፈሳዊነታችንን የቀበረ፥ ሞራላችንን የሰበረ፤
የልታወቅ ባይነታችንን ስሜት ያሳበጠ፥
ሰብእናችንንም ያጎበጠ።
እንዲሁም የእርኩስ መንፈስ ሹክሹክታ - እንደ ጋኔን መሳብ፥ ሚርትና ምታት ማሳየት ያለው፥
እምነትን የሚያሰናክል፥ ልዩነቶችን የሚያበዛ፥ ከብርሃን ወደ ጨለማ የሚከተው፥
ክፉው እስከ ዛሬም ከእኛው ጋር ነው ያለው - ጥሩ መስሎ እየተላለፈ ከአንዱ ወደሌላው።
ሰማያዊ መንፈሳዊ እውቀት - በነእስማዚያ ያልተበከለው፥
በገዛ አይምሮአችን እድገት ሊገኝ ይችል ነበር - መጥፎውን በመራቅ ጥሩውን ብንቀርበው፤
ግን በእርኩስ መንፈስ ተንኮል - የረከሱ መላእክትንም ወሬ እየሰማን ነው ያደግነው።
ስለዚህ፥ ስንኩል እውቀቶችን ይዘንም ነው የምንጉኣዘው።
ይህንን ከግንዛቤ ማስገባት ነው የዘመኑ ሰው የተሳነው።
አይ! ...እኛ ሰዎች ሞኞች ሆነናል፥ ራሳችንን ማየት አቅቶናል፤
በውስጣችን ክፋትና ተንኮል ነግሦብናል፤
አንዳንዶቻችንም፥ ምሁራን የተባልን ሳይንቲስቶች፥ በገዛ እውቀቶቻችን ታውረናል፤
ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰባችንም ከዘለኣለማዊ እውነታዎች አርቆናል።
አዳምና ሔዋንን ያስከዳ፥
ሰውን ከፈጣሪው የለየ- በኃጢአት ግርጊዳ፤
የሰውን ተፈጥሮኣዊ ማንነቱን እያሳጣ፥ ሳያቋርጥ የሚሠራ፤
ብሎም የራሱ ዜጋ ሊያደርግ፥ ሰውን ወደ ልዩ አለም እየመራ።
ከየአቅጣጫው - ከህጻን እስከ አዛውንት፥
የከፋ የከረፋ ምክሩን የሚሰማ እንዲበዛለት፥
ተፈጥሮአዊ ሂደትን መቀለስ - ሰይጣናዊ አለምን ለመመሥረት፤
ይህ አለማወቅ፥ የሰይጣንን አላማና ግብ አለመረዳት፥.........
ይህንን የመሰለ፥ የሁለት አለም ፍትጊያ በጠበጠን፥
ለይተን ባላወቅነው አለም፥ እየታየን ሳይሆን እየመሰለን እንኖራለን፤
በስመ ሥልጣኔ - እውቀት ወጥመድ ሆነብን፤
ቋኣንቋኣችን፥ ባህል ወጋችን፥ ዘፈን መዝሙራችን፥ እንዲሁም ዳንሳችን፥
ፊደላችን ሳይቀር ትምህርታችን፥ ሁሉን ጠልተን ከራሳችን ተደበቅን።
ጥቂቶችን ለርሱ ሞኝ የሆኑትን - እያነሆለለ፥ በኛ ላይ ብልጦች ያደረጋቸዋል፤
ጌታ የማይወደውን መጥፎውን፡- “እዎ! እንደሱ...ጥሩ እኮ ነው፥.. በሉ..በሉ” ይላቸዋል፤
እነኚህም ብልጦች ለነርሱ ሞኝ የሆኑትን ወደ ጥፋት ይመሯቸዋል።
ለአንድ ምስኪን ሰው እልፍ አእላፍ ሆኖ አሳሳች መንፈስ ይቀርበዋል፥
በዚህም ምክንያት፡- ፍቅር፥ ሰላም፥ ጤንነትና ደስታን አጥተን ቆይተናል።
ግን ዛሬ፥ በፈጣሪ አምላካችን በእግዚአብሔር ተማምነን፥
ጠላታችንን - የክፋት መንፈስን፥ “ሂድ - ከእኔ ውጣ” ለማለት ቆርጠን ተነሳን፤
ለዚህም፡- ስንጸልይ የምትጸልይ አብራን - የምታማልደን፥
ወላዲተ እምላክ - እምዬ ማርያም አለችልን - ምስክራችን፤
ሳንፈራ እንጸልያለን፥ ተራዳኢ መላእክትም አሉ ከጎናችን።

## ጉልህ ሆነው ከሚታዩት ከውርስ እውቀቶች መካከል ጥቂቶቹ

እውቀት አንጻራዊ፥
በጊዜ ውስጥ ተለዋዋጭ ታዳጊ፤
በእውነታዊነቱ ተጨባጭ፥
በርቀቱ ስሜታዊ።
የእውቀት አንጻራዊነት የማይካድ ቢሆንም፥
ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ብናውቅም፥
በእውቀቶቻችን ውስጥ ውሸት የነገሠበት እውቀት አይታጣም።
ለምሳሌ ከሃይማኖት ቀጥ ያለው - እውነታው እያለልን፥
ምድራዊ ስነአመክኖአዊ አመለካከትን እንቀላቅላለን።
እንዲሁም ከሳይንስ - ንፁሁ ሳይንስ - የማይታበለው ሃቅ እያለልን፥
ኢሳይንሳዊ በሆነ ትምህርት ጊዜ እናጠፋለን።
በክፋት መንፈስ የስበት ኃይል ውስጥ ስላለን፥
ለፈጣሪ የሚያቀርበውን - ከፈጣሪም የሚያርቀውን መለየት ተሳነን፤
በቅዱስ መንፈስ አንድ መሆን አቅቶን ተለያየን።

ከቶራ እስከ አዲስ ኪዳን፥
ከግሀቫታ ጊታ እስከ ቁርአን፥
ሁሉም የመንፈስ መድኃኒት እንዳይሆን፥
ሰዎችን በሃሳብ የሚከፋፍል፥
አንድነታቸውን የሚያሳጣ ተንኮል፥
መነሺያውን እና ሂደቱን እናስተውል።

ነገሮችን ሳናጎላ - የእውነት አንጻራዊነቱንም ባለመርሳት፥
የቀድሞ ክርስቲያኖችን መከፋፈል እንኩኣን ብንመለከት፥
ተለይቶ እናያለን - ቅልጥጥ ያለው ውሸት፥ ከሃቀኛው እውነት።

ከትውልድ ትውልድ አልበርድ ብሎ የነስማዚያ መንፈስ፥
ታላቅ ትግል ተካሂዶ ነበር፥ የክርስቲያኖችን እንድነት የሚያደፈርስ፤
በአንድ በኩል ቅዱስ አትናቴዎስ - በሌላም በኩል እርኩስ አርዮስ።

የሃይማኖት እድገቱን ካመጣጡ ለሚያስተውል እንደእምነቱ ይሁንለት፤
እርኩሱ አርዮስ ግን በአደባባይ ነበር የተዋረደው፤ ቅልጥጥ ያለ ውሸት በዝቶበት[13]፤
ከርሱ ቀጥሎም ይኸው እስከዛሬ - በጊዜ ውስጥ ሁሉ ጨኸት፥
አንድ ላይ ሆነን እንዳንቀድስ በኣርዮስ በኩል የተጠነሰሰ ክህደት፥
በክርስቲያኖች አለም፥ የዶግማ ልዩነት፥
ለያይቶ አስቀመጠን እንዳይኖረን ህብረት።

አርዮስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው (ፍጡር) ነው እንጂ፥ አምላክ አይደለም ሲለን፥
በቁጥር ስንት እንሆን? አሜን ብለን የክርስቶስን እግዚአብሔርነት የካድን።

ግን በቅዱስ አትናቴዎስ የነገሠው እውነት ሲከሰት፥
የፈጣሪያችንን ዘለአለማዊ ፍቅር የሚያመለክት፥
እንዲሁም የሚያባባ ሰብአዊ - ልባዊ ፍቅር ያለበት፥
ፈጣሪያችን እራሱን ዘንበል አርጎ፥ የገዛ እናቱን ለኛ የሰጠበት፥
እኛም ደስ ብሎን እናታችንን የወሰድንበት፤

---

[13] አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ ኣበባ።

ይኸው እስከዛሬ፥ በጸሎተ ሃይማኖት[14] የጸና እምነት፤
ካቶሊኮችም ኦርቶዶክሶችም የሚጸልዩት።
በሃይማኖት ፍልስፍና ውስጥ ገብቶ ለመዋዠቅ ሳይሆን፥
በእውቀቶች መካከል ጣልቃ የሚገቡትን፥
የከፉዎች መናፍስትን ሥራ ለማጋለጥ፥ ይህንን አልን።
የክርስቲያኖች መለያየት በየቤቱ ሰላምና እረፍት ቢያሳጣም፥
እስካሁን አለም አቀፋዊ ጦርነትን አላስከተለም፤
የሥልጣኔአችን ቀደምት የሆነው፥ የጦር መሳሪያ ግንባታ ግቡን አልመታም፤
ለሃይማኖታዊ ጦርነትም በቂ ድጋፍ አላገኘም።
ግን የጦር መሳሪያ ግንባታ፥ አላማና ግቡን የሚያይበት፥
ሲጠባበቅ ቆይቶ - አቀጣጣይ እሳት፥
ስለ እውነት ልግደልና ልሙት ባይ ከተፍ አለለት - የእስላም ሃይማኖት፤
የእስላሞች ወረራ ተከናወነ ሰባት ጊዜያት።
አሁንም አለም አቀፋዊ የእስላሞች ወረራ ይሰበካል፤
ግን ሰላማዊ የሆኑ - ብዙሃኑ እስላሞች እምቢ ብለዋል።
ጥቂቶችን ለርሱ ሞኝ የሆኑትን - ቢመራቸውም፥
የእስላምን ሃይሞኖት እንደልቡ ሊጫወትበት አልቻለም፤
ጠላት እየገፋ ገደል አፋፍ ቢያደርሰንም፥
እውነቶችን ሁሉ ችሎ አይጥላቸውም።
በሳይንስም ተጨባጩን እውነት ባንክድም፥
ወደ ክህደት የሚያመራውን መለየት አላቃተንም።
ለምሳሌ፡- በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን፥ ቻርለስ ዳርዊን የሚሉት ሰው፡-
ሳይንሱን ከፀረ አምልኮ ፍልስፍና ጋር ሲያዋህደው፥
የእርስ በርስ ግንኙንትን በጊዜ ውስጥ ወደኋላ ሲመልሰው፥
የዘር መደቦችን (species) በማመሳሰል አንድ አደረጋቸው፥
ሰውንም ከእንስሳ አዛመደው።
ዳርዊን ያለፈውን - እንዲህ ነበር ሕይወት ብሎ አወሳልን፤
ጊዜ ነፍሳማ አካላትን ረጋግጦ ያለፈውን፤
እያነበበ የቅሪተ አካላቱን፥ በዝቅጠ አለታት የተመዘገቡትን።[15]
ግን ያላሰብነውን - አንድ የስነ አመክንዮ አስተሳሰብ ቀበረልን፤
"መለወጥና መገኘት እንጂ፥ መፈጠር የለም" አለን።[16]
የጦር መሳሪያ ግንባታ - የሥልጣኔአችን ቀደምት፥
ራሱን አጎልብቶ ሲጠባበቅ፥ ሌላ አቀጣጣይ እሳት መጣለት፤
የሃይማኖት ልዩነትን የሚያስንቅ፥ ከእሳትም እሳት - ሳይንሳዊ እሳት፥
የነእስማዚያ ልጆችም ደስ አላቸው፥ በሳይንስ የተደገፈ አምልኮ ነውና የመጣላቸው፤

---

[14] http://media.wix.com/ugd/a268ea_270a85fecefa426081a81b5e564bbee1.pdf

[15] ከምድራዊነታችን ባሻገር፥ ቅጽ ሁለት፥ ምዕራፍ 5 - ከዚሁ ድረ ገጽ።

[16] ከምድራዊነታችን ባሻገር፥ ቅጽ ሁለት፥ ምዕራፍ 6 - ከዚሁ ድረ ገጽ።

እናንተስ የ“ዝግመተ ለውጥ”[17] ቀደምት – ልዩዎች ሆናችሁአል አላቸው።
ያ የርሱ የአንትሮፖሎጂ ጥናት፥ ትንቢቱና ግምገማው፥[18]
ለወረራ ተመቻቸው።
ከሰሜን ያሉትን - ነጫጮቹን ለይቶ፥ ወደ ላይ ከፍ - ከፍ አደረጋቸው፤
ከደቡብ ያሉትንም - ጥቁአቁሮቹን ለይቶ፥ አጣጣላቸው፤
ዘረኞችም የጥናቱን ውጤት ተመርኩዘው፥
በአስተሳሰብም አንድነትን መሥርተው፥
ለግድያ፥ ለወረራ፥ ለብዝበዛ ተመቻቸው፤
ጥቁሮችን እንደእንስሳ፥ እራሳቸውን እንደ መላእክት ቆጥረው፤
“እኛ ነን ከሰውም በላይ” አሉ፤ አለምን በቅኝ ግዛት ይዘው።
የዳርዊን ትንቢቱ በከፊልም ቢሆን ሰመረለት፤
ብዙዎቻችንን ጨረሱን በጦር ኃይል ብዛት፤
ግን ማን መለወጥ ይችላል፥ የተፈጥሮን ሂደት?
በአለም ታዋቂ ሆኗልና፤ የሰው ልጅ እኩልነት።
ሃቀኞች ሳይንቲስቶች[19] ሃቀኛውን ሳይንስ ይዘው ዳርዊንን አጋለጡት፤
በዚች ምድር - የሚመሳሰል ነገር በበዛበት፥
በማመሳሰል ብቻ አይገኝምና እውነት፤
አብሮ አይሄድምና፤ ሳይንሳዊነት እና ስሜታዊ አስተያየት።
እህ!...በቁጥር ስንት እንሆን?
ዳርዊንን ተከትለን - እግዚአብሔር የካድን።
የዳርዊንን ሥራዎች አንድ ባንድ ለመንቀፍ ሳይሆን፥
በእውቀቶች መካከል ጣልቃ የሚገባውን፥
የከፋት መንፈስን ሥራ ለማጋለጥ ስንል፥ ይህንን አልን።
ጥሩውና መጥፎው ሳይንስ በውጤቱ ይታወቃል፤
ጥሩው ሳይንስ ደስ ይላል፥ በሥጋ አጥግቦ መንፈስን ያረካል፤
መጥፎው ግን ያስጠላል፥ ከፈጣሪም ያጣላል፤
መንፈስን ያስጨንቃል፥ በመጨረሻም ያጋድላል።
ሰው ከፍቅርና ከእውነት የመነጨ እውቀቱ ሲያስደስተው፥
ከጥላቻና ከውሸት የመነጨ እውቀቱ ነው የቀበረው፤
ጥሩው እውቀቱ ባንድ ጎኑ ራሱን ሲጠቅመው፥
መጥፎው እውቀቱ ነው ወደ ክፋት የመራው።
ገና ከልጅነታችን፥ ማንነታችንን ወደሚያሳጣ ትምህርት አመራን፤
ስናድግ የሆነውን ትተን፥ ያልሆነውን ሆንን።
ከትምህርት ቤት በሚመነጭ የዘመኑ እውቀት ተመርቀን፥

---

[17] Evolution

[18] “…………..At some future period not very distant as measured by centuries, the civilized races of man will almost certainly exterminate and replace the savage races throughout the world…….” Charles Darwin, in "The Descent of Man, 1871" - ለወደፊት የሰለጠነው የሰው ዘር (ነጩ ማለት ነው) በአለም ዙሪያ ያሉትን ሁኣላ ቀሮች (ሳቬጆች) ያጠፏቸውል።”

[19] የነኚህን ሃቀኞችና ታዋቂ ሳይንቲስቶች ሥራ (ለምሳሌ - Fazale Rona & Hugh Ross, 2004 እንዲሁም 2010) አንባቢ ይመልከት።

የውጪያዊ ማንነታችን መታወቂያችንን ይዘን እንዞራለን።
አወቅን ብለን እንጮሃለን፥ መንፈሳዊው እኛነታችን እየተናነቀን፤
ራሳችንን ስናታልል፥ ማወቅን ስንታገል፥ የሰሜኑን፥
የደቡቡን ረስተን ደስታ ጭፈራውን፥
ግራ የተጋባን ልዩ - ተጨናቂ ፍጥረታት ሆነን(?)፥ እንደየብጤአችን።
ከኛው - ከአብራካችን ከወጣ፥ ከሄኖክም አንሰማ አልን፤
ትምህርት ማሳወቁን አንጂ፥ አላማና ግቡን አላየን፥
በተገንጣይ መላእክት እውቀት እውቀታችንን ቀየረን፤
በፀረ ፈጣሪ ትምህርቶቻቸው ሳቢያ፥ መንፈሳችንን ከመንፈሳቸው ቀላቀለን፤
ምድራዊ ብቻ በሆነ ፍልስፍናዎቻቸው ተገታን፤
እነርሱ ያሳወቁንን - ያወቅነውን ሆንን (መምሰል ብቻ ሳይሆን)።
አንዳንዴም ያ ያወቅነው (ያወቅን የሚመስለን) ጭራሽ ማንነታችንን እያሳጣን፥
በውዳሴ ከንቱ እርስ በርስ እየተሞካከሸን፤
በትእቢት እና በኩራት እንወጠራለን።
ከሉሚናቲ - ከጥፋት ውሃም በፊት፥
እነኚያ ከደብረ ቅዱስ የመጡብን፥ የረከሱ መላእክት፥
በአለማችን የሰለጠነ መጥፎነትን ጨመሩባት (ወሰኩባት - አከሉባት)።
ሳይንሱ ከጦር መሳሪያ ግንባታ ነበር የጀመረው፥
እስከ ዛሬም ድረስ ከመከላከያ በመነጨ ሳይንስ ነው የሚመራው፤
ምድራችንን አጥፍቶ ጠፈርን መውረር ነው መጨረሻያው።
የነርሱ ልጆች - ኔፊሊም (ግዙፋኖቹ)፥ ዘር ተከተው ባያልፉ፥
አሁንም ልጆቻቸውን (?) ነጥቀው ለመውሰድ (???) እንዲህ ባልለፉ (???)።
ዘመነ ኦሪትን ተሻግሮ፤ ዘመነ ሐዋርያትን ነካክቶ፤
ሃይማኖትን አጥፍቶ - ወይንም ለተንኮል እንዲመች ተመቻችቶ፥
አለም አቀፋዊ ስርዓትን መስርቶ፥...
ምድሪቱን ለጥቂት ብልጥች - ሃብታሞች ሰጥቶ፤..
ይህ ገመድ? የአለምን ሕዝብ በተንኮል የሚያስር፥
ይህ ታላቅ ሴራ - የነእስማዚያ ምስጢር፥
በጥቂት የሃብታሞች ክበብ አለምን ለማስተዳደር፤
ከዚህም አልፎ ከሳይንቲስቶች በመመሳጠር፥
የሚካሄደው ምርምር፥ በላቦራቷር፥
እንደሰው የሚያስብ አንስሳ ለመፍጠር፥
እንዲህ ይከሰታል፥ የሰውና የክፉ መንፈስ ትብብር።
ሰውማ ከጥንቱ፥ ከአንድ ሥፍራ (ኢትዮጵያ) ተጀምሮ፥
ሲሰደድ - ሲሰደድ - እዚያና እዚያ ተንሸራሽሮ፥
በንግድ ልውውጥና በመቀራረብ አንዱ ከሌላው ተምሮ፥....
የሰው ማንነትም አንደየሁኔታው ተለዋውጦ፥
በምድራዊነቱ - በኢኮኖሚው ይዘት፥ ወይንም በጉብዝናው፥ ሰላሙን ማስከበሩ በጦርነት፥
ስልጣኔም የእውቀት መስፋፋት፥
ሰው በብዛት ከሠፈረበት - የክፋት መንፈስም በታጨቀበት፤.............
እህ! ከጥንት ጀምሮ እስካሁን፥ የአላማ እና የግብ፥ የእኛ እና የእነሱ ልዩነት፥
ባንድ በኩል ለጽድቅ ለእውነት፥ በሌላም በኩል ለኃጢአት - ለውሸት።
እውቀታችን ከክፉ መንፈስ አብሮ፥

ልዩ አይነት እውቀትን ፈጥሮ፥….
እህ!...የሰሜኑን ወርቅ መሳይ ብልጭልጭ ባናይ ነበር የሚሻለን፥
እንደበፊቱ ብንኖር ይሻለን ነበር - እራሳችንን በራሳችን ተጠቃለን።
ከአንድ የሸረኞች ምንጭ ባይሆን ኖሮ፥ ሥልጣኔ የመነጨበት፥
ሌላ አይጠፋም ነበር፥ ልዩ የሥልጣኔ አይነት፤
ከአጀማመሩ መጨረሺያውም የሚያምርለት፤
ምድሪቱን በጢስ የማያፍናት፤
በሉላዊ የሙቀት እድገት ውሃዎቹአን የማያፈላባት፥
በስባሽ በሆኑ ሬዲዎ ኑክላይድ የማያቃጥላት፤
በመጨረሻም ሕይወት አልባ መሬት የማያደርጋት።
ግን እኮ እኛም መጠየቅ ያለብን - የሰሜኑን ከደቡቡ ምን ለየው?
የትኛውስ ስልጣኔ ነው ይህች ምድር በራሷ ያፈራቺው?
የትኛውስ ነው ከውጪ የመጣው?
አንዳንድ ሰዎችም የአለም አቀፍ አርኪዎሎጂ ጥናቶችን አካሂደው፥
ከዘቀጡ አለታት ውስጥም ቅርሳቅርሶችን ሰብስበው፥
የአትላንቲስ - የሳሃራ እና የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካንም ሥልጣኔ አገናኝተው፥
የምድራችን ስልጣኔ የተሰባበረ መሆኑን ተናግረዋል አጽንተው።
ያም ሆነ ይህ፥ ለምድራችን የሚያስፈልጋት የሥልጣኔ አይነት፡-
ውሃ፥ አፍርና አየር፥ እጽዋት፥ እንስሳና ሰው በአንድነት፥
ባለ ሕይወት - ሕይወት አልባም ተስማምቶ የሚኖርባት።
ለጥፋት የማይውል - ሳይንስንም የምንማርበት፥
በመንፈስም ሥራ ምድሪቱን የሚያለመልማት፥
ሁሉም በተናጠል ሳይሆን፥ በተዋህዶ እውቀት፥
ተፈጥሮአዊ ማንነቷን የሚጠብቅላት - የሚንከባከባት።
የሰው ልጅ በችሎታው ከጥሩ ተነስቶ መራቀቅ ሲቻለው፥
ወደ ክፋት ማምራቱ ነው እጅግ የሚያሰጋው።
ግን፥ እግዚአብሔር ለጠፈር ሕሊናን ሰጥቶታል[20]፤
በጊዜ ውስጥ የመንፈስና የአካል ሽርሽሩ ይቀጥላል፥
ከጠፈራዊ ሕግ ወጥቶ ማን ምን ማድረግ ይችላል???
ተመስገን - እስከ ዛሬ ሳንጠፋ ከዚህ ደረስን፥
በኃይለ መስቀሉ እየተጠበቅን፤
ለወደፊትም፥ ጌታ አለልን፥
የ“አንድ ኣድርገን” ጸሎታችንን የሚሰማን፥
ፍቅር፥ ሰላም፥ ጤንነትና ደስታን የሚሰጠን።

## <u>የስነ አመክኖአዊ አስተሳሰባችን ነጻነት</u>

እስካሁን የጠቃቀስናቸው፥
እንዲሁም ሌሎች እውነትን ስንፈልግ የምናወሳቸው፥
ከእውነታዎች ኣንጻር ስናያቸው፥
እውነትነታቸው ቢያጠራጥሩንም፥

---

[20] ከምድራዊነታችን ባሻገር፥ ቅጽ ሁለት፥ - ምዕራፍ 8፡ ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና።

የውጪ ኃይላት እንዳሉ አንክድም።
ብዙዎች ናቸውና፥ የሰማናቸው አይተንም ላለማመን ያስቸገረን፥
ሕይወታችንን ያተረማመሱብን፥
የደረሱብንም ችግሮች ብዙዎች ናቸውና፥ ይህንን አልን።

አንዳንዶቻችንም፥ እናትና አባታችንን ለመምሰል እንኳን ጊዜ አላገኘን፥
ገና በልጅነት ተነጥቀን ለምድራዊነት ተሰጠን፤
ምድራዊነትም የማናውቀው - ልናውቀውም የማንችለው - የማይገባን ሆነብን፤
በሰው ላይ ሰው ጠላት ሲሆን አይተን ደነገጥን፤
በሄድንበት የምናየው ግፍና ኃጢአት መሥራት አስፈራን፤
ስናድግ ያንኑ የፈራነውን - ምድራዊነትን መሰልን፤
ሳንወድና ሳንፈቅደው የገባንበት በመሆኑ ምንም አልተመቸን፤
በምድራዊ እውቀታችን ገንዘብ ሸምተን፥ በድሎት መኖር ሲቻለን፥
አልፈቅድ አለ መንፈሳዊነታችን፤
መሆን ከነበረብን ውስጣዊ ማንነታችን ጋር እየታገልን፥[21]
አንዳንዴ አውቀን አንዳንዴም ሳናውቅ ኃጢአት እየሠራን፥
እንዲሁ እንኖራለን፥ ማንነታችንን በምድራዊነት ለውጠን።

ውስጣዊ ማንነታችን በፍለጋ ሆነን፥ እራሳችንን ስላጣን፥
የመንፈስ መታወክ - እስከ አይምሮ ህመም እንደርሳለን፤
ካለ ቅዱስ መንፈስ ምንም መድኃኒት የለም የሚያድነን።[22]

እስቲ ማን ያውቃል? ከውጪ (ክፉ መናፍስት) ካለማቋረጥ ቢሰብኩን፥
በስነ አመክኖአዊ አስተሳሰባችን ጣልቃ እየገቡ ቢጨቀጭቁን፤
በብቸኝነት የማሰብ ነጻነታችንንም ቢያሳጡን።
እስቲ ማን ያውቃል? ከምናየው (ከምድራዊነታችን) ባሻገር፥
አካላዊ ያልሆነ አለም ቢኖር።
ማን ያውቃል? የኛ አካላዊ ሆኖ መኖር፥
ለነርሱም ቢሆን የህልውናቸው ድንበር።

እውቀታችን (በተለይ ዘመናዊው) ከአንጎላችን ሰፊውን ሥፍራ ስለያዘብን፤
መታየት - መታወቅ ያለበትን ነው የሰወረብን፤
የክፋት መናፍስት በቁማችን ሲጫወቱብን፥
የገዛ እውቀታችን የክፋት መናፍስትን መኖር እንዳናውቅ አደረገን።

ይልቁንም ታላላቅ የተባሉ ሳይንቲስቶችን፥ የአገር መሪዎችን በእጅ አዙር ሲወስዱብን፥
አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎችንም የራሱ ሲያደርግብን፥
በርኩሳን መናፍስት እየተመራን መሆናችንንም አላወቅን።

አይምሮስ ምንድነው ካለመንፈስ ብቻውን፥
እንዴት ሊያውቅ ይችላል ሁሉን?
አንጎልም ነገር የሚቋጥር ነተራ፥
የሚመመገበው እውቀት ካልጠራ፥

---

[21] “ድካምንና ጣርን አይ ዘንድ፥ ዘመኔም በእፍረት ታልቅ ዘንድ፥ ስለ ምን ከማኅፀን ወጣሁ?” ኤር. 20፥11

[22] “አቤቱ ተመለስ፥ ነፍሴንም አድናት፥ ስለ ቸርነትህም አድነኝ።” መዝ. 6፥4፥ “ፊትህን በባሪያህ ላይ አብራ፥ ስለ ምህረትህም አድነኝ።” መዝ. 31 (30)፥16 “አቤቱ አምላኬ እርዳኝ፥ ስለ ምሕረትህም አድነኝ።” መዝ. 119 (118)፥4

ወደ ጥፋት - ወደ ገደል ነው የሚመራ።
የአንጎል ሕዋሳትም ጠባየ ፍጥረታቸው ልክ እንደ ጠፈሩ፤
ግሊአል የተባሉ ሙጫዎች፥ እርስ በርሳቸው የተጣመሩ።
አንጎል፡- በመልእክት አስተላላፊዎች፥ የነርቭ ሕዋሳት ሰራዊቱ፤
ኢሌክትሮ ኬሚካል ንዝረቱ፥ የሚገመት - የሚለካ፥ እድገቱ፥ ክሳቱ፤
ቢበላ አይታይ ሙብላቱ - ቢተፋ አይታይ ትፋቱ፥
እሳተ ግሞራ ስሜቱ - የምድር ተምሳሌት በማንነቱ፤
አቤት! ጥልቀቱ - የእውቀቱ! የቃላቱ - ብዛቱ፥
የቋንቋው - ስፋቱ፥ ሌትና ቀን ሲፈራረቁበት - ራሱን መሳቱ፥
በዳግማዊ ባቢሎን ቅዠቱ፥ ባርነቱ ለምድራዊው እውቀቱ፤
ነፃነቱ፥ ሕሊናው ንቃቱ፤ እስከ ጠፈር ግዛቱ።
መጫወቺያ ኳስ የሌላት ድመት፥
በገዛ ጭራዋ እንደምትጫወት፥
ሰውም ከራሱ እውቀት ጋር በጫወታ ብዛት፥
ልዩ እውቀት በውስጡ ነገሠበት።
ታዲያ፥ የሰው አይምሮ ብቻውን፥ የድርጊቶች ሁሉ ተጠያቂ ቢሆን፥
ከፉውንና ደጉን ከየት እያገኘ ይሆን???
ግዙፉን ከደቂቁ አገናኝተን፥
ሁሉ ነገር ከሁሉ ነገር ይያያዛል ካልን፥
የመንፈስንም (ሁለቱም አይነት) አንለይም ማያያዙን፥
አጣብቂኝነቱን - የሚታየውን - የማይታየውን።
ከአካል - ከነፍሱ በምድራዊነቱ፤
ሲሞትም ከነሰማያዊ ነፍሱ በሕይወቱ - በሕያውነቱ።
እንዲሁም፥ በጠፈር ውስጥ ሁሉ ነገር እርስ በርሱ ከተሳሰረ፣
አንጎልንም ኣይዞህ የሚለው አይጠፋም፥ ከውጪ ኃይል ከተባበረ።
ታዲያ - ምድራዊና ሰማያዊ እውቀት ከተያያዙ፥ የሰው አንዱ ባሕርይ ሆነው፥
ማን ያውቃል? ለእውቀትስ መጥፎነት - ሰይጣናዊነት ቢኖረው።
ምስኪኖችም - ድሆችም አንድ የማያወላውል እውቀት <u>አለ</u> በውስጣቸው፤
እነርሱ ሲከፋቸው የሚከፋው፥ ደስ ሲላቸውም ደስ የሚለው፥
ከጠፈራዊ ሕሊና አንድ ኃይል እየተሰማቸው፥
አጽናኝ መንፈስ ቅዱስ መኖሩን አውቀዋል በእምነታቸው።
ሕሊና ያለን፥ እኛ ሰዎች ብቻ ባንሆንም፥
ጠፈራዊ ሕግጋት መኖራቸውን አንክድም።
ሰውማ (ነጭ፥ ጥቁር፥ ቢጫ)- ምን ክፋት ሊኖረው ይችላል ብቻውን፥
አበለሻሽቶት እንጂ የውጪ ኃይል - አንጎሉን - አይምሮውን።
ሰው በዘመናት ሁሉ ባንድ ጎኑ ጥሩው እውቀቱ ራሱን ሲጠቅመው፥
በሌላ ጎኑ መጥፎው እውቀቱ ነው ወደ ገደል እየመራው ያለው።
ታዲያ ማነው ይህንን ደስ የሚል ሰው የደበቀው?
እነኛ የነስማዚያ ተከታዮች ግን - በዙሪያችን የከበቡን፥
ውሸት እና ኃጢአትን በተሞላ ፍልስፍናቸው አጨማለቁን፤
በስግብግብነታቸው በከሉን፥
እርስ በርሳችን ሲያገዳድሉንም እንደ በግ ዝም አልን፤
መጥፎው ገሸሽ ብሎ፥ ጥሩው ሲመጣ ለማይየት ያብቃን።

## ከዘመኑ እውቀት ባሻገር

የሄኖክ ምክር ዋና ግልጋሎቱ፥ ከጥፋት ውሃ ለነበሩ ሰዎች ቢሆንም፥
ሰይጣን ምድሪቱን የርሱ ግዛት ለማድረግ ማሰቡን አልተወም፤
የዘመኑ እውቀት አመጣጡ፥ ከሰው የአይምሮ እድገት ጋር ቢያያዝም፥
በውስጡ ለክፋት - ለጥፋት ተስተካክሎ የተቀመጠ ተንኮል አይጠፋውም፤
ምንም እንኳን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፈቃድ እውቀትና ጥበብ ቢያገኝም፥
በውስጡ ለክፋት የሚውል ሰይጣናዊ እውቀትም  በውስጡ አይታጣም፤
በዚህም የዘመኑ ስልጣኔ በማር የተለወሰ መርዝ ሳይጨመርበት አልቀረም።

በብዛትም ባይሆን በከፊል፥ የውጪ እውቀትም ይሆናል ኢትዮጵያን የተናነቃት፤
ፍቅሯን፥ ሰላሟን፥ ሕብረቷን እና አንድነቷን የቀማት፤
የያዘቿውን - የጨበጠቿውን - የርሷ የሆነውን ሁለ የአስጠላት።
እኛም ቅድስት ኢትዮጵያን ማየት አቃተን፤
የምድራዊ እውቀት ስነአመክንዮ ሰፊውን ሥፍራ ስለያዘብን፥
መንፈሳዊውን ስነአመክንዮአችንን ስለደበቀብን።

ሰማያዊ አሰራር ሳይገባን፡-
“ይህማ ሊሆን ኣይችልም...” እንላለን፤
በቅድሚያ አምነን ሁሉን ማወቅ ሲቻለን፥
በዚሁ በምድራዊ አመለካከታችን ተወስነን፥
በክህደት አለም ውስጥ ብዙ ቆየን።
እነርሱን (የክፋት መናፍስትን) ግን ዝም አልን፤
እነርሱም በእጅ አዙር ጠቀለሉን።

እስቲ ማነው? ማነው ኢትዮጵያዊ?  - በአለም ዙሪያ ተመላልሶ ሁሉን ያስተዋለ፤
የራሱን የሆነውን ሁሉ ጥሎ፥ ሌላውን መሆን የቻለ።
ይህንንስ እንኳን እኛ ከኢትዮጵያ የተወለድን፤
ከውጪ የተወለዱትም አልቻሉትም - ልጆቻችን።

ስለዚህ፥ ከዘመኑ እውቀት - ከምድራዊነትም ባሻገር፥
ልቦናችን - ውስጣዊ ማንነታችን ይክበር፤
ኢትዮጵያዊነት ነው ተከባብሮ መኖር።

ሰው ምንድነውና ብቻውን?... ሰው እንዴት ያውቃል ራሱን?
ሌላውን ሳይመስል -  ወይም ሳይሆን።
ሰውማ ብቻውን፥ መሪ ያጣ ደንባራ፥ ተከትሎ ሌላውን - ሰው የመሰለውን፥
እጁን አይቶ - ሰጪውን፥ እግሩን ተከትሎ - መሄጃውን፥
ንግግሩን ሰምቶ - ልፈፋውን፥ መጽሐፉን አንብቦ - ፍልስፍናውን፥
ትምህርቱን ተከታትሎ - ያስተማሪውን፥
እንደ ትያትረኛ እንደ ተዋንያን፥ ራሱን ጥሎ ሌላውን እንደሚሆን፥
እንደ ሕልም አላሚ - ከራሱ ተነጥሎ እንደሚኩአትን፥
ልዩ አለም ውስጥ እንደሚገባ ብኩን፥ መጨረሺያውን ሳያውቅ የሚፋጠን።

እስቲ በሉ እንጂ!  እንሰብስብ እራሳችንን፥ ከፍ ከፍ እናድርግ ልቦናችንን፤
አለን ጥበብ በየአይነቱ - ከቤታችን፤
ቆንጆ ነው ባህላችን፥ ወግ ማዕረጋችን፥ ጨዋነት፥ ደግነት፥ አንድነት ፍቅራችን፤
በቅድስት ኢትዮጵያ (ኤርትራ) አገራችን።

ይህ የዛሬው ፍቅር የተለየው እውቀት ሲደፈርስ፥

ፍቅርን ያዘለ ሰማያዊ እውቀት[23] ሲቀሰቀስ፥
ትምህርት እንደገና እንደ አዲስ፥ ሀ ብለን አቡጊዳ - መልእክተ ዮሐንስ፤..........
እግዚአብሔር እንዲሁ አለምን ወዷልና እያልን፤....
ከሳይንሱም እንዲሁ ለሰው ልጅ ጠቃሚውን እየለየን።

  የኛ የኔታ ተግተው ያስተማሯቸው፥ ጠግበዋል በጾማቸው ፤
  ተደስተዋል በማጣታቸው፥ አጊጠዋል ባላቸው።
  በአይን ቅጽበት ደርሰዋል ከግባቸው።

## ኃይልና ሥልጣን የእግዚአብሔር ነው

በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፥ አንድ አምላክ። አሜን።
ሁለን በፈጠረ በእግዚእብሔር አምላካችን አምነን፥
በወላዲተ አምላክ አማላጅነት፥ በመላእክት፥ በጻድቃንና ሰማእታት ተራዳኢነት አምነን፥
ፍቅር፥ ሰላም፥ ጤንነትና ደስታን እንማጸናለን።

  እንደነሱ (የክፉት መናፍስት) ይህም ጽሑፍ አላማና ግብ አለው፤
  በእውነት ኃይልና ሥልጣን የእግዚአብሔር ነው፤
  ድኅነትን ለሚሻው፥ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምላሽ አለው።[24]

    ስለዚህ፥ ሰው ሆይ! አትፍራ፤ እራስህን አታሳንስ፥ እውቀት የለኝም ብለህ፥
    እውቀትና ኃይል የእግዚአብሔር ነውና፤ ሁሉንም ከእርሱ ታገኘዋለህ።
    በአካል ግዑዝ - በመንፈስ ሕያው - ባለ ሕሊና ጠፈራችን፤
    እኛ በጊዜ ውስጥ እዚህ ነን፤ እኛም በጊዜ ውስጥ ከዚያም ነን፤
    ግን ምንጊዜም፥ የእግዚእብሔር መንፈስ አይለየን።

በክፉ መንፈስ ምክንያት፥ ፍቅር፥ ሰላም፥ ጤንነትና ደስታን አጥተን ተንገላታን፤
ግን ዛሬ፥ በፈጣሪ አምላካችን በእግዚአብሔር ተማምነን፥
<u>የዘወትር ጸሎታችንን[25] </u>እየጸለይን፥
ጠላታችንን - የክፉት መንፈስን፥ “ሂድ - ከእኔ ውጣ” እንላለን፤
ለዚህም፡- ስንጸልይ የምትጸልይ አብራን - የምታማልደን፥
ወላዲተ እምላክ - እምዬ ማርያም አለችልን - ምስክራችን፤
ሳንፈራ እንጸልያለን፥ ተራዳኢ መላእክትም አሉ ከጎናችን።

  ከእንግዲህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደኅንነትን፥
  መንፈሳዊ አንድነትንም አግኝተን፥
  ውስጠ ማንነታችን አስከብረን እንኖራለን።
  ለዚህም ቸሩ አምላካችን እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

## ጸሎት

ጠብቀህ ከዚች ሰዓት ያደረስከን፥

---

[23] “ላኛዪቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፤ በኊላም ታራቂና ገር፥ እሺ ባይ፥ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት።” ያዕ 3፡17

[24] “ለምኑ ይሰጣችሁኣልም፥ ፈልጉ ታገኛላችሁም፥ ደጅ ምቱ ይከፈትላችሁኣልም።” ማቴ 7፡7

[25] http://media.wix.com/ugd/a268ea_a1aef37949e4480b9eb4220b3f25afd9.pdf

ቸሩ እግዚአብሔር አምላካችን ክበር ተመስገን፤
የምታድነን አምላካችን አንተ ነህና አትለየን።
እቤቱ! ከእለት ህኪት - ከክፋት መንፈስም ሰውረን፤
ከሚያስጨንቁን፥ ከችግሮቻችን ሁሉ አላቀን፤
ፍቅር፥ ሰላም፥ ጤንነትና ደስታን አታሳጣን፤
በብርሃንህ እንመላለስ ዘንድ፥ በመንገድህ ምራን፤
ውዷቷ አገራችንን ኢትዮጵያን ጠብቅልን።
አሜን።

## መደምደሚያ

ሰፋፊ ባሕረ ሃሳቦችን እንዳው ጠቃቀስናቸው፤ ተመራማሪ ወስዶ ይመርምራቸው።
ስለ መንፈስም ጉዳይ ለጻድቃን እንተወው፤ የቅዱስ መንፈስ ኃይል ለተሰጣቸው፥
እነርሱ ናቸውና በግልጽ የሚታያቸው፥ በብርሃን ስለሚመላለሱ - ከደንባራው አለም ወጥተው።

መቼም መጥፎው ሳይታይ ጥሩው አይመጣም፤
እንዳው እግዚአብሔር ጣልቃ ባይገባም፥
ጥሩውና መጥፎው አብሮ ብዙ አይዘልቅም፤
ጎላ ብሎ የሚታይ ኃያል ሁሉ ሲወድም፥
ለጽድቅና ለእውነት የቆመ ሥልጣኔ መብቀሉ አይቀርም።

እውነቶች ከያለበት ሲገመዱ፥ በቅንነት የተሞሉ፥
ዘረኛነት - ተእቢትና ኩራት ብቻቸውን ይቀራሉ፤
የዛን ጊዜ፥ ሰዎች ሁሉ ድንቁርና የወጣለት እውቀትን ያገኛሉ።

ሰዎች ስለሆንን፥ ባንወጣም፥ ከምድራዊነታችን፥
አጭር ብትሆንም፥ ክቡር ናት ሕይወታችን፤
የረከሱ መናፍስት ሰለባዎች እንዳንሆን፥
እንዳናጣው መንፈሳዊነታችንን - እንዳንወጣ ከሙሉ ሰብአዊነታችን፥....

የውጪ እውቀት የኢትዮጵያን በማጣጣል (ወይም በመተካት) አይሁን፤
ከማወቅ ጋር ድንቁርናም እንዳያድግ እየተጠነቀቅን፥
መጥፎ መጥፎውን (ጎጂና ጎታቹን) እያስወገድን።
ጥሩውን ብቻ ይቅሰም አይምሮአችን፤
እውቀት በጥንቃቄ - ፍቅርን መሳቢያ - ሌላውን መንከባከቢያ፥
እንዳይሆን ራስን ማሳበጪያ፥ ሌላውን ማሳነሺያ - ማጣሊያ - ማባረሪያ፤
እውቀት እንዳይሆን መዝለፊያ - መሳደቢያ - ሰውን መጉጃያ የጥፋት መሳሪያ።

ልጆቻችንም ከቤት አይውጡ ሳይመስሉ እኛን፥
ሳይማሩ ባህላችንን፥ እምነታችንን፤
ሁላችንም አንራቅ ከቤተ ክርስቲያን፥
መራቃችን ፍዳ እንዳያበዛብን - ያልሆነውን ሆነን።
አናቃልል መንፈሳዊ ትምህርታችንን፥
ምድራዊ ድንቁርናን የሚመክትልንን፤
ለአንድነታችን መሠረት የሚሆንልንን።

ከውጪው አለም ተለይተን ስለማንኖር፥
ግዴታችን ይሆናል፥ ከሌሎችም መማር፤
ግን፥ ምንጊዜም የእግዚአብሔር መንፈስ ይኑር ከኛ ጋር።
አሜን።አሜን።አሜን። ለዘለአለም።